መጋቢት 21 2003 ዓ.ም.

# <u>ከኢሮብ ለኤርትራ ስለተሰጠው መሬትና የአቶ መለስ አቋም!</u>

## ከኢሮብ መብት ተሟጋች ማህበር (ኢ.መ.ተ.ማ )

በየካቲት መጨረሻ አከባቢ ጠቅላይ ሚንስተር መለስ ዜናዊ አሰና.ኮም (asena.com) ለሚባል በትግርኛ ወደ ኤርትራ ለሚሰራጭ ረዲዮ ሁለት ሰዓት አከባቢ የፈጀ ቃለ-ምልልስ ሰጥተዋል። ቃለ-ምልልሱ ባጠቃላይ የኢትዮ- ኤርትራን ግኑኝነት በተመለከተ በርካታ ዝርዝር ነጥቦችን የያዘ ነው። ትግርኛ ቋንቋን መስማት የሚችል ሁሉ በዓይጋ ድረ-ገጽ አርካቭስ ውስጥ በመግባት ማርች 2011 በሚለው ሥር ቁጥር (2) በመጫን በግራ ረድፍ ላይ በሚታየው የአቶ መለስ ፎቶ ሥር ያለውን ቃለ-መጠይቅ ክፍል አንድና ሁለት ማድመጥ ይችላል ። አቶ መለስ ከአሰና ረዲዮ ጋዜጠኛ ጋር ያደረጉት ቃለ-ምልልስ በርካታ ሊተቹ የሚገባቸው ርእሰ ጉዳዮችን ያካተተ ቢሆንም ለዛሬ ቱኩረት ሰጥተን የምንመለከተው ስለ ኢትዮ-ኤርትራ ድንበር ማካለል የሚሉትን ነው። ስለሆነም ኢ.መ.ተ.ማ ባጠቃላይ ጉዳዩ የሚመለከተው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ደግሞ የኢሮብ ብሄረሰብ ተወላጆች አቶ መለስ ዜናዊ ስለ የኢትዮ-ኤርትራ ድንበር አከላለል አስመልክቶ ከአሰና ሬዲዮ (Asena.com) ጋር ያደረጉትን ቃለ-ምልልስ እንዲያዳምጡት ይጋብዛል።ለጥያቄዎቹ በሰጧቸው መልሶች የሀገራችን ዳር ድንበርና ሉዓላዊነትን አሳልፈው ለመስጠት መቁረጣቸውን በቀጥታና በግልጽ ቋንቋ ያሰፈሩት በመሆኑ ልብ ብለን እንድናዳምጠውና መውሰድ ያለብንን እርምጃ አሁኑኑ እንድንወስድ ኢ.መ.ተ.ማ. ከወዲሁ ያሳስባል።

ይህን እየተተቸበት ያለው ድንብራችንን በተመለከተ የአቶ መለስ ቃለ-ምልልስ ትግረኛ የማይሰሙትን ወገኖቻችን የውይይቱ ተሳታፊ ለማድረግ እንዲያመች የጋራ መግባቢያችን ወደ ሆነው የአማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ በጽሑፍ ቀርቧል። ለትርጉሙም ሃላፊነቱ ሙሉ በሙሉ የኢ.መ.ተ.ማ. ይሆናል።

ድንበርን በተመለከተ ለአቶ መለስ በትግርኛ የቀረበው ጥያቄ ወደ አማሪኛ ሲተረጎም እንደሚከተለው ይመስላል ፣

አሰና.ኮም፤

> ***"የኢትዮ-ኤርትራ ድንበርን በተመለከተ የግልግል ፍርድቤቱ ውሳኔ ሰጥቷል። በውሳኔው መሠረት የድንበር አካላይ ኮምሽን ድንበሩን ማስመሩና ሁለታችሁ መንግስታትም ያለ ምንም ተቃውሞ ውሳኔውን መቀበላችሁ የሚታወቅ ነው። ይህ በእንዲህ እያለ ግን በኢትዮጵያ መንግስት በኩል የድንበሩ ኮሚሽን ያሰመረው የድንበር መስመር ተቀብለናል ብትሉም ተግባራዊ ለማድረግ ግን ፈቃደኛ ሳትሆኑ ስለቀራችሁ፤ ይኸው እስከዛሬ የድንበር መስመር ተግባራዊ አልሆነም። ለምን ውሳኔውን እስከተቀበላችሁ ድረስ በውሳኔው መሰረት የድነበሩን መስመር እንዲሰመር ፈቃደኛ አልሆናቹህም?"***
> የሚል ነበር።

አቶ መለስ ለጥያቄው የሰጡት መልስ ሲተረጎም እንደሚከተለው በ6 ነጥቦች ይጠቃለላል ።

1. **"የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ወደድነውም አልወደድነውም ያለ ምንም ቅድመሁኔታ ተቀብለነዋል። እኛ እያልን ያለነው በፍርድቤቱ ውሳኔ መሠረት የድንበሩ አካላይ ኮምሽን ያሰመረው የድንበር መስመር እንዴት በመሬት ላይ ማስቀመጥ እንዳለብን እንነጋገር ነው ። ይህ ያልንበት**

ምክንያት ደግሞ አንዳንድ ቦታዎች ላይ የድንበር መስመሩ መንደሮችን አልፎ ቤቶችን ለሁለት ሰንጥቆ ስለሚከፍል፤ ይህን ዓይነቱን ችግር ተነጋግረን እንፍታ ነው።

2. እኛ በፍርድቤቱ ውሳኔ ላይ ተቃውሞ ቢኖረንም፤ ገና ከጅምሩ ውሳኔውን ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ መቀበላችን ለተባበሩት መንግስታት ጽ/ቤት በጽሁፍ አሳውቀናል።
3. ኮሚሽኑ እኔ በግሌ የማውቃቸው መንደሮች እንኳን ሳይቀር ለምሳሌ በፆረና አከባቢ የኤርትራ አካል የሆኑ፣ ኤርትራዊያን ነን ብለውም ከ30 ዓመት በላይ ለመብታቸው የታገሉ ሰዎች የሚኖሩባቸው መንደሮች ለኢትዮጵያ ሰጥቷል። በሌላ በኩል ደግሞ ሻዕቢያ የኢትዮጵያ መሬት መሆናቸውን በሚገባ የሚያውቃቸው መንደሮች ለኤርትራ ተሰጥተዋል።
4. በድንበር አካላይ ኮሚሽን ውሳኔ መሰረት ከኢትዮጵያ የተወሰዱትንና ከኤርትራ የተወሰዱትን መንደሮች በመነጋገር እኩል እንከፋፈል በሚል እኛ ያቀረብነው ሃሳብ አልቀበልም ያለው የሻዕቢያ መንግስት ነው።
5. ኤርትራን እንዳለ ሰጥተን አሁን አንድ ሁለት ወይም ሶስት መንደሮች ወደኛ መምጣት ለኛ ምንም አያደርግልንም። በኮምሽኑ ውሳኔ መሰረት ድንበሩን ለማካለል በኛ በኩል ዝግጁ ነን። እኛ እያልን ያለነው የድንበሩን መስመር በመሬቱ ላይ ለማስመር እንነጋገር ነው።
6. በሻዕቢያ በኩል ፈቃደኝነቱ ካለና ያቀረብናቸው 5ቱን የኖርማላዘሽን ውሳኔዎቻችን ከተቀበለ፣ የድንበር መስመር አከላለልና አፈጻጸሙ ላይ ለመነጋገርም ሻዕቢያ ዝግጁ ከሆነ አንዳንድ ማንገራገሮች በአንዳንድ አከባቢ በህዝቦች መከሰቱ እንኳ የማይቀር ቢሆንም፤ ይህን ሁሉ ተቋቁመን በኛ በኩል ለመነጋገሩም ሆነ ድንበሩን በኮሚሽኑ ውሳኔ መሰረት ለማስፈጸም ዝግጁ ነን” ነው አቶ መለስ የሚሉት።

ይህ ከላይ የተቀመጠው የአቶ መለስ ዜናዊ የኢትዮ-ኤርትራ ድንበር ምን እንደሚመስል፣ ምን ያህል መሬት እንደተወሰደ ያስቀመጡትን ከራሳቸው አንደበት ሲደመጥ አቶ መለስ ዜናዊ ከኢትዮጵያ ይልቅ ለኤርትራ ጥብቅናና ጥቅም የቆሙ ሰው ናቸው የሚለው በብዙ ኢትዮጵያዊያን የሚታሙበት አባባል ተራ ሃሜት ሳይሆን እውነትነቱ ቁልጭ ብሎ የታየበት ሃቅ እንደሆነ በማያሻማ መልኩ እየተገለጸ መሆኑ ነው። ለምሳሌ እዚህ ላይ በተራ ቊጥር ሶስት በከፊል ስለተጠቀሰው ጉዳይ ሲናገሩ፣ ከኤርትራ ለኢትዮጵያ ተሰጠ ስለ ሚሉት መሬት የአከባቢው ስም እየጠቀሱና ሺ ጊዜ ኢትዮጵያውያን አንዳልሆኑ ያስታወቁ ሰዎች ለምን በግድ ኢትዮጵያውያን ሁን ይባላሉ በማለት እጅጉን ተጨንቀው ሐዘናቸውን ይገልጻሉ። በዛው መጠን ግን የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ከኢትዮጵያ ለኤርትራ የተሰጡ መሬቶችን በስም መጥራታቸው ቢቀር ኢትዮጵያዊ ነኝ እያለ ወደ ኤርትራ ስለተካለለው ህዝብም ቢያንስ ተመሳሳይ ሐዘኔታ ማሰማት ይጠበቅባቸው ነበር። ያለ ፍላጎታቸው ወደ ኤርትራ እንዲከለሉ ስለተደረጉት የኢሮብና ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ለፆሮናዎች የተጨነቁትን ያህል እንኳ አልተጨነቁም። (የኤርትራ መሬት ነው ስለሚሉት ፆሮና በግልግል ፍርድ ቤት ክርክር ሲደረግ የአቶ መለስ ልኡካን ምን እንዳሉ በውሳኔው ውስጥ የተጠቃለለ ብዙም የተጻፈበት በመሆኑ ለጊዜው እዚህ መድገም አስፈላጊ አይሆንም) የሆነ ሆኖ አቶ መለስ ዜናዊ ጸረ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና አንድነት ለመሆናቸው በተለያየ ጊዜ በተግባር ያስመሰከሩ ሰው ስለሆኑ፤ እዚህ ላይ ይህንን ጉዳይ በመተቸት የአንባቢን ጊዜ ማባከን አስፈላጊ አይሆንም። እዚህ ላይ ባጠቃላይ አቶ መለስ ዜናዊ ከባድመ፣ ፆሮናና፣ ዛላምበሳ ግንባሮች በኩል ለኤርትራ ስለተሰጠው የኢትዮጵያ መሬት የተወሰኑ ትናንሽ መንደሮች ብቻ ናቸው የሚሉት ፈጽሞ ውሸት መሆኑ የገላጋይ ፍርድ ቤቱ ውሳኔን በመግለጥና የተሰመሩ ካርታዎችን በመመልከት ማመሳከር የሚቻል በመሆኑ በዚህ መግለጫ ዝርዝር ውስጥ መግባት አስፈላጊ ሆኖ አልታየንም።

የዚህ ሐተታ ዋና ትኵረትና ጭብጥ አቶ መለስ ዜናዊ ከኢሮብ ወረዳ ለኤርትራ የተሰጠው መሬት የተወሰኑ ቤቶችና ትናንሽ መንደሮች ብቻ ናቸው የሚለው አባባል ውኃ የማይቋጥርና ከእውነትም

የራቀ በመሆኑ እውነቱን ለኢትዮጵያዊያን ለማሳወቅ ነው። አቶ መለስ ዜናዊ በተለመደው እብሪታቸው ተጨፈኑና ላሞኛችሁ ሊሉን ቢፈልጉም የኢሮብ መሬትን በተመለከተ ለሁለት የተከፈለው የተወሰኑ መንደሮች ብቻ ሳይሆኑ **መላው አድጋዲ-ዓረና ለም የሆኑ ምዕራባዊ የቡክናይቲ-ዓረ ሉዓላዊ የኢትዮጵያ መሬቶች** ለኤርትራ እንደተሰጡ በመላው የኢሮብ ብሄረ-ሰብ በግልጽ ስለሚታወቅ ሊያሞኙን አይሞክሩ ልንላቸው እንገደዳለን። ኢ.መ.ተ.ማም የአቶ መለስን ተግባር በጽኑ እንደምቃወመው ግልጽ ከማድረግ አልፎ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በተለይም ጉዳዩ በቀጥታ የሚነካን የኢሮብ ተወላጆች ይህንን በሉዓላዊ ግዛቶቻችን ላይ የሚፈጸመውን ደባ ለማስቆም አሁንም ያላሰለሰ እንቅስቃሴ እንድናደርግ አክብሮት ያልተለየው ጥሪውን ያቀርባል።

በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው የኢህአዴግ መንግሥት ከኢሮብ መሬት በትክክል ለኤርትራ አሳልፎ የሰጠው ከየት እስከየት እንደሆነ የተለያዩ ጸሃፍት በተለያየ ጊዜ ለማሳየት ሞክረዋል። አቶ ሱመ በጥር ወር 2003 ዓ.ም በኢሮብ ማብሎ ድረ-ገጽ ( www.irobmablo.org ) ለኢሮብ ወጣቶች ስደት ሶስቱ መሰረታዊ ምክንያቶች በሚል ርእስ ባስነበቡን መጣጥፉ ውስጥ የድንበር አካላይ ኮሚሽን በሄግ በ2002 ዓ.ም.ፈ በሰጠው ውሳኔ መሰረት ከውሳኔው ጋር አባሪ የተደረገው ካርታ የሚያመላክተውን መስመር በመከተል ከኢሮብ ለኤርትራ የተከለሉ ቦታዎች የትኞች እንደሆኑ በመጠኑ ዘርዝር አድረገው አስቀምጠውልናል። ስለሆነም ከአቶ ሱመ መጣጥፍ ከኤርትራ ጋር ያለን ድንበር በኮምሽኑ ከተሰመረው መስመር በኋላ ምን እንደሚመስል፣ ምን ያህሉ መሬታችን እንደተወሰደ የሚያሳየውን ክፍል እንዳለ ለግንዛቤ እንዲረዳ ገልብጠን እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

ከአቶ ሱመ ጽሁፍ እጠቅሳለን፣ *"የኢትዮጵጰያ መከላከያ ሠራዊት በአከባቢው በመስፈሩ እንዴት ለወጣት የኢሮብ ሴቶች ከአከባቢው መሰደድ መንስኤ እየሆነ እንዳለ ከመዘርዘሬ በፊት በኢህአዴግ አገዛዝ ተቀባይነት ካገኘው ከሄግ ውሳኔ በኋላ ከኤርትሪያ ጋር ድንበራችን ምን እንደሚመስል ትንሽ ለማሳየት ይፈቀድልኝ። ይህንን የማደርገው አንደኛ እወቀቱና ችሎታው ያላቸው በዚህ ጉዳይ ላይ ይበልጥ ግልጽ መሆን ያለባቸውን በግልጽ በካርታ እያስደገፉ እንድያስቀምጡና ሁሉም እንዲያውቀው እንዲያደርጉ ለማሳሰብ ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እስከዛሬ ድረስ አዶሓ ኢሮብ እየተባለ ከሚጠራው አንደኛው ክፍል ማለት አድጋዲዓረና ብዙ መንደሮች ከቡክናቲዓረ ወደ ኤርትሪያ የተወሰዱበት ሁኔታ ላይ ስለሆን ይህ በሁሉም ጉዳዩ በሚመለከተው በግልጽ እንዲታወቅና መወሰድ ያለበት እርምጃ የድንበሩ ጉዳይ በማነኛውም በሚያደርጉት ስምምነት መሠረት ካርታ ተሰርቶ በዛ መሰረት በተግባር ከመሰመሩ በፊት ማድረግ ያለብን ሁሉ እንድናደረግ ለማሳሰብ ነው።*

*በአጠቃላይ ሁኔታውን ለማወቅና ለመቃወም ዕድል ባገኙ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ከፍተኛ ተቃውሞ የተደረገበትና በኢህአዴግ መንግሥት ብቻ ተቀባይነት ያገኘው የሄጉ ውሳኔ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ውሳኔው እንዲሻር የተቀነባበረ ትግል ካላደረግን <u>እስላምቶዳ፣ ዓጋራለ-ኮማ፣ቦሖሎ፣ ካረዳና ሌሎች የምዕራባዊ ቡክናይቲዓረ ሰፊ ለም መንደሮችና ድፍን አድጋዲዓረ የኤርትራ ይሆናሉ ማለት ነው።</u>*
(መስመር በኢ..መ.ተ.ማ የተጨመረ)

*የኢህአዴግ መንግስት መልሶ መላልሶ የሄጉን ውሳኔ እንደሚቀበል በተለያየ ሚዲያ ግልጽ ያደረገ ሲሆን አፈጻጸሙ ላይ ብቻ ከኤርትራ መንግስት ጋር ንግግር እንደሚፈልግ ነግሮናል። ይህ መነጋገር ያስፈለገበት ምክንያት ደግሞ የድንበሩ መስመር ሲሰመር አንዳንድ መንደሮችን ለሁለት የሚከፋፈልበት ሁኔታ ስላለ ይህን ለማስተካከል ብቻ እንደሆነ ጠቅላይ ሚንስተር አቶ መለስ ዜናዊ ደግመው ደጋግመው ነግረውናል። እዚህ ላይ ስለ ሌላው ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትሪያ የተወሰዱት ቦታዎች ብዙ ማለት ባልችልም ከኢሮብ መሬት ወደ ኤርትሪያ የተወሰደው ጠቅላይ ምንስተሩ እንደሚሉት የተወሰኑ መንደሮች ብቻ ሳይሆን እስከ ዛሬ ኢሮብን ሙሉ ኢሮብ ከሚያሰኙት መሬቱና ህዝቡ ከአንድ ሶስተኛ መሬትና ህዝብ በላይ እንዳለ ያለ ህዝቡ እውቀትና ፍላጎት ለኤርትሪያ*

***መሰጠቱን ነው። ይህን ሃቅ ሁሉም የኢሮብ ብሄረሰብ አባላትና መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በግልጽ ማወቅ ያለበት ጉዳይ ነው። የኢህአደግ መንግሥት እስከ ዛሬ በሄጉ ውሳኔ መሠረት ወደ ኤርትራ የተከለለውን መሬታችንና ህዝባችን ለሻዕቢያ ያላስረከበው ይህን ውሳኔ ተግባራዊ ቢያደርግ የኢትዮጵያ ህዝብና ሰራዊት እንደማይቀበለው ስላወቀ ብቻ ነው። ስለዚህ አሁን ይህ የሄጉ ውሳኔ እንዲሻር፣ የኢሮብ መሬትና ህዝብ ከጥንት ከጥዋቱ አባቶቻችን ያቆዩልንን ድንበር ይዞ እንዲቀጥል፣ እኛ ኢሮቦች ኢትዮጵያዊያን እንጂ ኤርትራዊያን እንዳልሆን መንግሥታችን በደንብ የሚያውቀው ጉዳይ ቢሆንም በግልጽ ደጋግመን ልንነግረው ይገባናል። ችግራችንን ደግሞ ሁሉም ኢትዮጵያና ዓለም አቀፍ ህብረተሰብ እንዲያውቁትና ከጎናችን እንዲቆሙም ጥሪ ማስተላለፍ መቻል አለብን። የኢህአዴግ መንግስት እስከ ዛሬ እንዳደረገው ሁሉ የድንበራችንን ጉዳይ በዝምታና በሽፍንፍን ይዞት እንዲቀጥል ፈጽሞ መፍቀድ የለብንም”*** ብሎ ነበር።

አቶ ሱመ ከላይ በግልጽ እንዳስቀመጡት የተወሰደብን መሬት የተወሰኑ ቤቶችና መንደሮች ብቻ የያዘ ሳይሆን ከአጠቃላይ የኢሮብ መሬት ከአንድ ሶስተኛ በላይ ነው። አቶ መለስ ዜናዊ ግን አሁንም ደግመው ደጋግመው፤ የተወሰዱብን የተወሰኑ መንደሮችና ቤቶች እንጂ፤ ሰፊ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛት የሆነው የኢሮብ ህዝብ የሚኖርበት መሬትና ህዝባችን በዚህ በሄጉ ውሳኔ መሠረት ወደ ኤርትራ መካለላቸውን ድሮም የሚደብቁት እንደሆነ ብናውቀውም፤ ዛሬ በአሰና ረዲዮ አማካይንት በትግርኛ ቋንቋ ግልጽና እንደሚገባን አድርገው በማያሻማ ቋንቋ ነግረውናል። ይህ ብቻም አይደለም፤ ሻዕቢያ አቶ መለስ ዜናዊ ባቀረቡለት 5ቱ የኖርማላዘሽን ውሳኔዎች መሠረት ለመነጋገር ፈቃደኛ ከሆነ ከህዝቡ በኩል የፈለገው እንቢተኝነትና ማንገራገር ቢኖርም የህዝቡን ማንገራገር እንደተለመደው በኃይል ጨፍልቀው መሬታችንንና ህዝባችንን አሳልፈው ለሻዕቢያ እንደሚሰጡ ግልጽ አድርገው አስቀምጠውልናል።ስለሆነም ጥያቄው አሁን እኛ ኢትዮጵያዊያን በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ የጉዳዩ የቅርብ ባለቤቶች የሆን ኢሮቦች ምን ማድረግ አለብን የሚለው ይሆናል።

በኢትዮጵያዊያን በአጠቃላይ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች ሊወሰዱ የሚችሉት እኛው የጉዳዩ ባለቤቶች የሆን ኢሮቦች ማድረግ የሚገባንን ስናደርግ ስለሆነ፤ እኛ ኢሮቦች የተወሰደብንን መሬታችንና ህዝባችንን በተመለከተ ከዚህ በታች የተቀመጡ እርምጃዎች ባንድነት ባስቸኳይ መወሰድ ይኖርብናል ብሎ ኢ.መ.ተ.ማ. ያምናል።

- ጣልያን ኤትርትራን ለ60 ዓመታት በቅኝ አገዛዝ ሲገዛ ወደ ተቀረው የኢትዮጵያ ግዛቶች ቅኝ አገዛዙን ለማስፋት ሲፈልግ በወቅቱ የኢሮብ ህዝብ ተጠሪ ለነበሩት ለቀማት ሲፋሪ ወልደገሪማ ኢሮብን በተለያየ ጥቅማጥቅሞች በመደለል እንዲከፋፍሉለት ሲጠይቃቸው፤ የአድጋዲዓረ ተወላጅ የነበሩ ቀማት ሲፋሪ ”ኢሮብ ቢርስን” **”ኢሮብን ለመከፋፈል መሞከር በምስር መካከል ልዩነት ለማየት እንደ መሞከር ስለሆነ አንድን ኢሮብ ከሌላው ኢሮብ ለይቼ ጥቅማጥቅም አገኝ ብዬ መናገር አልችልም”** ብለው እንደመለሱለት ከአባቶቻችን የተላለፈልን ሐቅ ነው። ስለሆነም እኛም የዛሬው ኢሮቦች እንደ አባቶቻችን በአንድነት ለአቶ መለስ ዜናዊና ለመንግሥታቸው ባለስልጣኖች ኢሮቦች ድንበራችንን በተመለከተ አንድ ነን፣ አድጋዲ-ዓረ፣ ቡክናይቲ-ዓረና ሓሳባለ አንድ ላይ ነው ኢሮብን ኢሮብ የሚያስብሉት፣ አሁን አድጋዲ-ዓረን ከቡክናቲ-ዓረና ሓሳባላ ለይታችሁ ወደ ኤርትራ ልትሰጡ ፈጽሞ አትችሉም፣ በዚህ በድንበር ጉዳይ ላይ የመንግስት ደጋፊና ተቃዋሚ ብላችሁ ልትከፋፍሉን ፈጽሞ አትችሉም ብለን በአንድ ድምጽ ለመናገር መቻል አለብን።
- አቶ ሩፋኤል ሲፋረ የወረዳው አስተዳዳሪ ለኤፍፒ ጋዜጠኛ ድንበራችን በተመለከተ የሰጡት መልስ የሁላችን ኢሮቦች መልስ መሆን አለበት። ስለሆነም በውጭ በስደት ዓለም ያለንም ሆነ በሀገር ቤት ያላችሁ፤ አቶ መለስ ዜናዊ አሁን በአሰና ረዲዮ ድንበራችንን በተመለከተ

የተናገሩትን የማንቀበለው መሆናችንን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አጥብቀን ልንነግራቸው ይገባል።

- እንደ አንድ አናሳ ብሄረሰብ ህልውናችንን ሊያጠፋ የሚችል የመከፋፈል እርምጃ በገዛ መንግሥታችን ተብዬ እየተደገሰልን መሆኑን ለዓለም አቀፍ የአናሳ ብሄረሰቦች መብትና ህልውና ተሟጋች ድርጅቶች ማሳወቅና እርዳታ መጠየቅ መቻል አለብን።
- ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን፤ በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው መንግሥት እያደረሰብን ያለው ችግር በአጠቃላይ፣ በተለይ ደግሞ ከጥንት ከጥዋቱ ጀምሮ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ አካል የነበረው የኢሮብ ህዝብ የሚኖርበት የኢትዮጵያ መሬት ከህዝቡ ፍላጎት ውጭ አቶ መለስ ዜናዊ ለኤርትራ አሳልፈው እየሰጡ መሆናቸውን በማሳወቅ፣ እንደ አናሳ ብሄረሰብ ዳር ድንበራችን ለማስከበር በምናደርገው ትግላችን ከጎናችን እንዲቆሙ መጠየቅ አለብን።
- ለኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት፤ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ወንድሞቻችን ውድ ህይወታቸውን የገበሩለት መላው አድጋዲ-ዓረና በርካታ የቡክናት-ዓረ መሬታችን በአቶ መለስ ዜናዊ ለኤርትራ መሰጠቱን በግልጽ በማሳየት ሰራዊቱ ከጎናችን እንዲቆምና ዳር ድንበራችንን በህዝቡ ፍላጎትና ውሳኔ መሠረት ህዝብንና ዳር ድንበርን የመከላከል ግዳጁን እንዲወጣ ጥሪ ልናስተላልፍለት ይገባል።

አባቶቻችን እስከዛሬ አስከብረው ያቆዩት አዶሓ ኢሮብ ተብሎ የሚታወቅ መሬታችን አይከፋፈልም!!!

ዳር ድንበራችንን ለማስከበር በአንድንት እንነሳ!!!

**ማሳሰቢያ ለሁሉም አንባቢያን፣** ይህ አንብቦ ዝም መባል ያለበት ጉዳይ ስላልሆነ እያንዳንዱ አንባቢ አቋም እንዲወስድበት፣ መደረግ ያለበትም በየአከባቢው እንዲያደርግ በጥብቅ ለማሳሰብ እንወዳለን። እንዲሁም ይህንን መግለጫ እያባዛችሁ ኢንተርነት የሌላቸው እንዲያገኙት እንዲታደርጉ አደራ እንላለን። አንብቦ ማስነበብ ትልቅ ሥራ ነው።

ኢ.መ.ተ.ማ